
# የመ/ሠ/ማ/ዋ/ኤ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን

# ለመከላከልና ለመቆጣጠር

# የወጣ ማንዋል



አዲስ አበባ

2013

## Conten


መግቢያ ........ iii

ክፍል አንድ ........ 1

ጠቅላላ ድንጋጌዎች........ 1

1. አጭር ርእስ........ 1

2. ትርጓሜ........ 1

3. የተፈፃሚነት ወሰን ........ 2

ክፍል ሁለት ........ 3

የተከለከሉ ተግባራት እና የተጣሉ ግዴታዎች........ 3

4. የተከለከሉ ተግባራት........ 3

5. የተጣሉ ግዴታዎች ........ 3

በስብሰባ ወቅት መወሰድ ስላለባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች........ 5

6. የተሰብሳቢዎች ብዛትን በተመለከተ ........ 5

7. ስብሰባውን የጠራው አካል መውሰድ ስለሚገባው የጥንቃቄ እርምጃዎች........ 5

8.ስብሰባውን የሚያስተናግደው መስተንግዶ ሰጪ አካል መውሰድ ስለሚገባው የጥንቃቄ እርምጃዎች ........ 6

9. የስብሰባ ታዳሚ መውሰድ ስለሚገባው የጥንቃቄ እርምጃዎች........ 7

10. የተቋሙ ሃላፊዎች መውሰድ ስለሚገባቸው ጥንቃቄ እርምጃ ........ 7

11. የተቋሙ ሠራተኞች መውሰድ ስለሚገባቸው ጥንቃቄ እርምጃዎች........ 7

ክፍል ሶስት........ 8

12. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች........ 8

13. ማንዋል ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ........ 8

## መግቢያ

ኮቪድ 19 በዓለም አቀፍ ደረጃ በፍጥነት እየተሰራጨ እና ከፍተኛ ጉዳት እያዳረሰ ያለ ወረርሽኝ ሲሆን ይህ ወረርሽኝ በሀገራችንም ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ይሄንኑ ወረርሽን ለመቆጣጠር እና መከላከል ያስችል ዘንድ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት መመሪያ 30/2013 እንዲጣጠም ሆኖ ይህ ማኑዋል በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ቫይረሱን በስራ ቦታ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ወቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርእስ

ይህ ማኑዋል "በመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ ማኑዋል ቁጥር 1/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ማኑዋል.

2.1 "**ኮቪድ-19**" ማለት በአለም የጤና ድርጅት በይፋ በዚህ ስም የሚጠራው ተላላፊ በሽታ ነው፣

2.2 "**አካላዊ መራራቅ**" ማለት የኮቪድ19 በሽታ ከሰው ወደ ሰው የሚኖረውን ስርጭት ለመቀነስ ወይንም ለመግታት በሁለት ወይንም ከዛ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ወይንም ሁለት ሜትር እና ከዛ በላይ ርቀትን መጠበቅ ነው፣

2.3 "**ስብሰባ**" ማለት ማንኛውንም ተግባር ለመፈጸም፣ ለመነጋገር፣ ስልጠና ለመስጠት፣ ለመወያየት፣ ግንዛቤ ለማስጨበጥ፣ ወይም መሰል ተግባራትን ለማከናወን የአንድ ቤተሰብ አባላት ከሆኑ ውጪ አራትና ከዚያ በላይ ሆኖ በአንድ ቦታ በአካል መገኘት ነው፣

2.4 "**የቤት ውስጥ መቆያ**" ማለት መኖሪያ ቤት ሆኖ በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖር በሚያስችል መልኩ መስኮት ወይም አየር ማስገቢያ ያለው እና ለኮቪድ 19 በሽታ የተጋለጡ፣ የተጠረጠሩ ወይንም ተመርምረው በበሽታው መያዛቸው የተረጋገጡ ሰዎች የሚቆዩበት ስፍራነው፣

2.5 "**ምልክት የሌለው የኮቪድ-19 ታካሚ**" ማለት ምንም አይነት የበሽታውን ምልክቶች የማያሳይ በኮቪድ-19 የተያዘ ሰው ነው፣

2.6 "**የኮቪድ-19 ምልክቶች**" ማለት በኮቪድ-19 የተያዘ ሰው ላይ ሊስተዋሉ የሚችሉ እንደ ትኩሳት፣ የራስ ምታት፣ የሳል፣ ጣዕምና ሽታን መለየት አለመቻል፣ የጉሮሮ አካባቢ ቁስለቶችና የመሳሰሉ ምልክቶች ናቸው፣

2.7 "RT PCR" ማለት በሞለኪዉላር ቴክኒክ የኮሮና ቫይረስ ምርመራ ስርዓት ነው፣

2.8. “RDT” ማለት ፈጣን የ ኮቪድ 19 የምርመራ አይነት ነው፣

2.9. **“ኮቪድ 19 ፖዘቲቭ”** ማለት በRT PCR ወይም ሌሎች ቫይረሱ በሰውነት ውስጥ መኖሩን ሊያሳዩ በሚችሉ የምርመራ አይነቶች ቫይረሱ የተገኘበት ሰው ማለት ነው፣

2.10 . **“ኮቪድ 19 ኔጌቲቭ”** ማለት በRT PCR ወይም ሌሎች ቫይረሱን በሰውነት ውስጥ መኖሩን ሊያሳዩ በሚችሉ የምርመራ አይነቶች ቫይረሱ ያልተገኘበት ሰው ማለት ነው፣

2.11 . **“ጸረ ተህዋሲያን ውህድ”** ማለት ከኮሮና ቫይረስ ጋር ንክኪ ይኖርቸዋል ተብሎ የሚታሰቡ እቃዎች ለማጽዳት የሚውል ከአልኮል ወይም ክሎሪን የተዘጋጀ ውህድ ማለት ነው፣

2.12 **“ክልል”** ማለት በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 47 የተመለከተ ወይም የተመሰረተ ማንኛዉም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደሮችም ይጨምራል፤

2.13 **ቅ/ጽ/ቤ/ት** ኤጀንሲው ለአሰራር እንዲያመች የከፈታቸው በሪጅን ስር የሚገኙ ጽህፈት ቤቶች ነው

2.14 **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ነው፣

2.15 **“ሠራተኞች ”** ማለት በመስሪያ ቤቱ የሚሰሩ ሰዎች ማለት ነው፣

2.16 **“ተገልጋይ “** በመስሪያ ቤቱ አገልግሎች ፈልገው የሚመጡ የውስጥና የውጪ ሰዎች ማለት ነው

2.17 በወንድ *ፆታ* የተገለጸው አነጋገር የሴትንም *ፆታ* ያካትታል፣

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ማኑዋል የኤጀንሲው አመራርና ሠራተኞች እና ወደ ኤጀንሲው አገልግሎት ለማግኘት የሚመጡ ተገልጋዮች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል::

## ክፍል ሁለት

### የተከለከሉ ተግባራት እና የተጣሉ ግዴታዎች

### 4. የተከለከሉ ተግባራት

4.1 ማንኛውም ኮቪድ-19 ያለበት ሰው ቫይረሱ እንዳለበት እያወቀ ወደ መስሪያ ቤት ውስጥ መግባት፣ ከሰራተኛው ጋር መቀላቀል ወይም ቫይረሱ ወደ ሌሎች ሰዎች ሊተላለፍ በሚችልበት ሁኔታ ከሌሎች ሰዎች ጋር መገናኘት የተከለከለ ነው፣

4.2 ማንኛውም ሰው ለሰላምታና ሌላ ለማንኛውም አላማ በእጅ መጨባበጥ፣ ሆነ ብሎ የእርስ በእርስ አካላዊ ንክኪ ማድረግ የተከለከለ ነው፣

4.3 ማንኛውም ሰው የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ ቀሪ መሆኑ እስከሚወሰንበት ጊዜ ድረስ ከመኖርያ ቤት ውጪ በማንኛውም ቦታ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ሳያደርግ መገኘት ወይም መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው፣ ሆኖም ዕድሜያቸው ከስድስት አመት በታች የሆነ ህጻናት ወይም በማስረጃ የተረጋገጠ የመተንፈሻ አካላት ወይም መሰል ችግር ያለባቸው ሰዎች ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚ አይሆንባቸውም፣

4.4 የተቋም ሰራተኞች ከሁለት የአዋቂ እርምጃ በታች ተጠጋግተው እና የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ሳያደርጉ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣ ተገልጋዮች በሚቀመጡበት ጊዜም ይሁን በማንኛዉም አኳኋን አገልግሎቱ ሲያገኙ ከሁለት የአዋቂ እርምጃ በታች ተጠጋግተው እና የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ሳያደርጉ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ወይም በአንድ ጠረጴዛ ከሶስት ተገልጋዮች በላይ እንዲቀመጡ ማድረግ የተከለከለ ነው፣

4.5 አገልግሎት በሚሰጥባቸው ቦታዎችና ሌሎች ህዝብ በሚበዛባቸው መሰል አካባቢዎች ከሁለት የአዋቂ እርምጃ በታች ርቀት መቆምም ሆነ መቀመጥ የተከለከለ ነው፣

4.6 ማንኛውም የህጻናት ማቆያ ማዕከል አገልግሎት መስጠት እንደሚቻል ሳይወሰን እንዲሁም አገልግሎት የሚሰጥበት ሁኔታ በተመለከተ በመመሪያ* የሚወጡ ሊወሰዱ የሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሳያከብር አገልግሎት መስጠት አይችልም።

### 5. የተጣሉ ግዴታዎች

5.1ማንኛውም ኮቪድ 19 በሽታ አለብኝ ብሎ እራሱን የሚጠረጥር ሰው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት በማድረግ የመመርመርና ቫይረሱ ወደ ሌሎች እንዳይተላፍ አስፈላጊውን ጥንቃቄ የማድረግ ሀላፊነት አለበት፣

5.2 በሽታው አለበት ተብሎ የሚጠረጠር ሰው ስለመኖሩ የሚያውቅ ማንኛውም ሰው በአቅራቢያ በሚገኙ የጤና ተቋም ወይም ባለሞያ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፣

5.3 አጠቃላይ አገልግሎቱን ለማግኘት ወደ ተቋሙ ለሚመጡ ተገልጋዮች በዚህ ማኑዋል ወይም የሚመለከተው ዘርፍ በመመሪያ በሚያወጣው የጥንቃቄ እርምጃ መሰረት ቫይረሱን ለመከላከል የሚያስችሉ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳሶችን የማቅረብ፣ ተገልጋዮች ሁለት የአዋቂ እርምጃ ተራርቀው የሚቆሙበትን ቦታ ምልክት የማድረግ እና ተገልጋዮች የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረጋቸውን እና ሌሎች አስፈላጊ ጥንቃቄዎችን መተግበራቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፣

5.4 ለኤጀንሲው ሰራተኞች ስለበሽታው አስፈላጊውን መረጃ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የማድረስ፣ በመግቢያና መውጫ በሮችና ሌሎች አስፈላጊ ቦታዎች በሽታውን ለመከላከል የሚያስችሉ አስፈላጊ ነገሮችን የማዘጋጀት ፣ የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የሚረዱ የጥንቃቄ ቁሳቁሶችን የማቅረብ፣ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረጋቸውን እና ሌሎች አስፈላጊ ጥንቃቄዎችን መተግበራቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው፣

5.5 በተቋሙ ማንኛውም የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ሀገር አቀፍም ሆነ የከተማ ውስጥ ትራንስፖርትን በተመለከተ በህግ ከሚወሰነው የመጫን አቅም ልክ ሰዎችን የመጫን፣ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ያላደረጉ ሰዎችን አገልግሎት አለመስጠት፣ መስኮቶችን በመክፈት በተሽከርካሪው ውስጥ በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖር የማድረግ እና በዘርፉ በመመሪያ የሚወጡ ሌሎች መወሰድ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች በመተግበር አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፣

5.6 በየደረጃ ያሉ የተቋሙ ኀላፊ ስለበሽታው አስፈላጊውን መረጃ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የማድረስ፣ በመግቢያና መውጫ በሮችና ሌሎች አስፈላጊ ቦታዎች በሽታውን ለመከላከል የሚያስችሉ አስፈላጊ ነገሮችን ማዘጋጀት፣ የስራ ቦታዎችን በቂ የአየር ዝውውር ሊኖርበት በሚችል መልኩ የማደራጀት፣የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የሚረዱ የጥንቃቄ ቁሳቁሶችን የማቅረብ፣ ሰራተኞች የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረጋቸውን እና ሌሎች አስፈላጊ ጥንቃቄዎችን መተግበራቸውን የማረጋገጥ፣ እንዲሁም ሌሎች ዘርፉ በመመሪያ*1 የሚያስቀምጣቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

5.7 በኤጀንሲው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ተጋላጭነትን ለመከላከል፣ ዝግጁነት ለማረጋገጥ እና ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታን በተመለከተ በዘርፉ በመመሪያ*2 የሚወሰኑ የጥንቃቄ እርምጃዎች የማክበር እና የማስከበር ግዴታ አለበት

*1የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስተር እና የኢትዮጵያ የህብርተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የሚያወጡት መመሪያ

*2 የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስተር እና የኢትዮጵያ የህብርተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የሚያወጡት መመሪያ

## በስብሰባ ወቅት መወሰድ ስላለባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች

### 6. የተሰብሳቢዎች ብዛትን በተመለከተ

6.1 በዚህ ክፍል የተዘረዘሩትን እና ስብሰባን ማካሄድን በተመለከተ በተዘጋጀው ማንዋል ላይ የተካተቱትን የጥንቃቄ እርምጃዎች አሟልቶ ያለተጨማሪ ፈቃድ እስከ 50 ሰው ሆኖ መሰብሰብ ይቻላል፣

6.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (6.1) ላይ የተቀመጠው እንዳለ ሆኖ ከ50 ሰው በላይ መሰብሰብ ግዴታ ሆኖ ከተገኘ ስብሰባው ሊደረግበት የታሰበበት አዳራሽን ጠቅላላ ስፋት ከግምት ውስጥ በማስገባት ቦታው ሊይዝ ከሚችለው ሰው ብዛት አንድ አራተኛውን በማይበልጥ ሰው ልዩ ፈቃድ ከሰላም ሚኒስቴር እና በተዋረድ ባሉ የክልል፣ ዞን እና ወረዳ የሰላም እና ፀጥታ መዋቅሮች አስቀድሞ በማግኘት ሊከናወን ይችላል

### 7. ስብሰባውን የጠራው አካል መውሰድ ስለሚገባው የጥንቃቄ እርምጃዎች

7.1 የግድ ካልሆነ በስተቀር በአካል የሚደረጉ ስብሰባዎችን ከማመቻቸት ይልቅ በተቻለ መጠን በኦንላይን አማራጮች ስብሰባዎች እንዲካሄዱ ማድረግ፣

7.2 ስብሰባውን በሚጠራበት ጊዜ ስብሰባው በተሳታፊዎች መሀል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ያህል (2ሜትር) ለመጠበቅ በሚያስችል አዳራሽ ከ50 ሰው ሳይበልጥ መካሄድ መቻሉን የማረጋገጥ፣ የእጅ መታጠቢያ ወይም ከአልኮል የተዘጋጀ የእጅ ማጽጃ (ሳኒታይዘር) በበቂ መዘጋጀቱን የማረጋገጥ እና ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው ማንዋል የተዘረዘሩ ሌሎች የጥንቃቄ እርምጃዎችን የመተግበር ግዴታ አለባቸው፣

7.3 ለስብሰባ የሚጠሯቸውን ተሳታፊዎች ስለኮሮና ቫይረስ በሽታ መተላለፊያ እና መከላከያ መንገዶች እንዲሁም በስብሰባ ወቅት ሊከተሏቸው ስለሚገቡ የጥንቃቄ እርምጃዎች በቂ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለባቸው::

## 8.ስብሰባውን የሚያስተናግደው መስተንግዶ ሰጪ አካል መውሰድ ስለሚገባው የጥንቃቄ እርምጃዎች

8.1 የስብሰባ አዳራሾች በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖራቸው የማድረግ፣ የእጅ ንጽህናን ለመጠበቅ የሚያስችሉ በቂ ግብዓቶችን የማዘጋጀት፣ በተቻለ መጠን የተሰብሳቢዎች መግቢያና መውጫ የተለያየ እንዲሆን የማድረግ፣ ተሰብሳቢዎች የሚጠቀሙባቸው እና በተደጋጋሚ የሚነኩ ቁሳቁሶችን ቢያንስ በቀን ሁለት ጊዜ ጸረ ተህዋሲያን ውህድ የማፅዳት፣ እና ሌሎች በተዘጋጀው ማንዋል የተዘረዘሩ የጥንቃቄ እርምጃዎችን የመተግበር ግዴታ አለባቸው፣

8.2 የእያንዳንዱን ተሳታፊ ስም፣ስልክ እና አድራሻን መዝግቦ እስከ 14 ቀን ድረስ በፋይል የማቆየት እና በ14 ቀን ውስጥ በበሽታው የተያዘ ወይንም የተጠረጠረ ሰው ከሌለ መረጃውን የተሳታፊዎችን የግል መረጃ ሚስጥራዊነት በጠበቀ መልኩ የማስወገድ፣

8.3 ስብሰባው በተሳታፊዎች መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ያህል (2 ሜትር) ተጠብቆ ከ50 ሰው ሳይበልጥ ስብሰባ የማካሄድ፣ እያንዳንዱ ተሰብሳቢ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ካላደረገ ስብሰባ ወደሚደረግበት ቦታ እንዳይገባ የመከልከል፣ እንዲሁም ከመግባቱ በፊት የሙቀት ልኬት የማድረግ ግዴታ አለበት፣

8.4 በስብሰባው ወቅት የኮቪድ-19 የጥንቃቄ እርምጃዎችን አወሳሰድ በተመለከተ የሚከታተል፣ የሚቆጣጠርና አስፈላጊውን እርምጃ የሚወስድ አንድ ሰው በቋሚነት የመመደብ፣

8.5 የኮቪድ ምልክት የታየበት ግለሰብ በአቅራቢያው ለሚገኝ የጤና ተቋም ወይም ባለሞያ የማሳወቅ ግዴታ እና በጊዜያዊነት ለማቆያ አገልግሎት የሚውል ለይቶ ማቆያ ክፍል ማዘጋጀት፣

8.6 ተሰብሳቢዎች በእረፍት ሰአት ወይም በምሳ ሰአት አካላዊ ርቀታቸዉን እንዲጠብቁ የሚያስችል ምልክት የማስቀመጥ እንዲሁም ሌሎች ከምግብ መስተንግዶ ጋር የተያያዙ አገልግሎች በሚሰጡበት ወቅት በተዘጋጀው ማንዋል የተዘረዘሩ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሙሉ በሙሉ የመተግበር ግዴታ አለባቸው::

## 9. የስብሰባ ታዳሚ መውሰድ ስለሚገባው የጥንቃቄ እርምጃዎች

9.1 የኮቪድ-19 ምልክቶች ካሳየ ማለትም የሳል፣ የሙቀት መጨመር ለመተንፈስ መቸገር ወይም ለኮቪድ 19 አጋላጭ ሁኔታ ውስጥ ከነበረ በበሽታው አለመያዙ እስካልተረጋገጠ ድረስ በስብሰባው አለመሳተፍ፣

9.2 ስብሰባው እስከ ሚጠናቀቅ ድረስ እንደምግብ ለመመገብ አይነት አስገዳጅ ተግባራት ውጭ በማንኛውም ጊዜ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል በአግባቡ የማድረግ፣ በስብሰባ ወቅት ጥያቄ በሚጠየቅበት እና ሃሳብ በሚሰጥበት ወቅት የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭንብሉን አለማውለቅ ወይም ወደ አገጭ ዝቅ ያለማድረግ ግዴታ አለበት፣

9.3 ከማንኛውም ሰው ቢያንስ በሁለት ሜትር አካላዊ ርቀትን ጠብቆ መሳተፍ፣እጅን ቶሎ ቶሎ መታጠብ ወይንም በሳኒታይዘር ማፅዳት፣ የተጠቀሙበትን ሶፍት እና ሌሎች የተጸዳዱበትን ቁሶች በአግባቡ ክዳን ባለዉ ቆሻሻ ማስወገጃ ማስወገድ፣ ስብሰባው ከተጠናቀቀ በኋላ የሚታደረው በዚያው በስብሰባው ቦታ ከሆነ በተቻለ መጠን በክፍል ውስጥ መቆየት እና ሌሎች በተዘጋጀው ማንዋል የተዘረዘሩ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሙሉ በሙሉ የመተግበር ግዴታ አለባቸው።

## 10. የተቋሙ ሃላፊዎች መውሰድ ስለሚገባቸው ጥንቃቄ እርምጃ

10.1 በጽ/ቤቱ ወይም በስራ ሂደቱ የሚገኙ ሠራተኞች የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል በአግባቡ ማድረጋቸውን መከታተል አለባቸው

10.2 የኮቪድ 19 ምልክቶች ከታዩባቸው ወዲያውን ፍቃድ በመስጠት ከሌሎች ሠራተኞች ጋር እንዳይገኛኑ ማድረግ አለበት

10.3 እያንዳንዱ ሠራተኛ በህመም ቀይቶ ሲመጣ የህክምና ማስረጃ መጠየቅ ይኖርበታል

10.4 ማንኛውም ሰራተኛ አገልግሎት ሲሰጥ የ2 ሰው የአዋቂ እርምጃ እርቀት እንዲሆን ምልክት ማድረግ ይኖርበታል

10.5 ማንኛውም የውስጥም የውጪም ተገልጋይ አገልግሎት ለማግኘት ሲመጡ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል ካደረጉ በአግባቡ ማስተናገድ ይጠበቅባቸዋል

## 11. የተቋሙ ሠራተኞች መውሰድ ስለሚገባቸው ጥንቃቄ እርምጃዎች

11.1 በሚሰሩበት መስሪያ ቤት ግቢና ቢሮ ውስጥ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል በአግባቡ ማድረግ ግዴታቸው ነው

11.2 ወረቀት ነክ የሆኑ ነገሮችን ከነኩ ከተቀበሉ ከሰጡ በኃላ እጃቸውን በሳኒታይዘር መቀባት አለባቸው

11.3 ማንኛውም የውጪ ሆነ የውስጥ ተገላጋይ ፊት የአዋቂ 2 እርምጃ እርቀት ተራርቆ ማስተናገድ ይጠበቅባቸዋል፡፡

11.4 በሰራተኛ ክበብ ውስጥ በአንድ ጠረጴዛ ከ 2 ሰው በላይ መቀመጥ የለበትም

11.5 ተቋሙ የሚያገለግሉ የትራንስፖርት አገልግሎት የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል ሳያደርጉ መግባት የተከለከለ ነው

11.6 የኮቪድ 19 ምልክቶች ከታዩበት ወዲያውኑ ለቅርብ ሃላፊ በማሳወቅ ወደ ህክምና ተቋም በመሄድ ተመርምሮ የቀረበትን ቀን የህክምና ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅበታል

## ክፍል ሶስት

### 12. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

12.1 የመተባበር ግዴታ ማንኛውም ሰራተኛ፣ አመራርና ፣ተገልጋይ ፣እና ተቋም ለዚህ ማንዋል ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

12.2 መመርያዎችና አሰራሮች በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የተለያዩ የዘርፍ መስርያ ቤቶች በየመስካቸው የሚያወጣቸው መመርያዎችና* አሰራሮች የኮቪድ 19 በሽታን ለመግታት ወይም ለመቀነስ በዚህ ማንዋል ውስጥ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች የማይቃረኑና ተጣጥመው የወጡ መሆን አለባቸው፡፡

12.3 የህግ ተጠያቂነት በዚህ ማኑዋል የተደነገጉ ክልከላዎችን እና ግዴታዎችን የተላለፈ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው የወንጀል ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 13. ማንዋል ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ ማንዋል ከ ------------------------------------------- ጀምሮ የጸና ይሆናል፤

የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የበላይ አመራር

ሚያዚያ 2013 ዓ.ም

*3 የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስተር እና የኢትዮጵያ የህብርተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የሚያወጡት መመሪያ